# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የጋራ ህንፃ /ኮንደምንየም ቤት/ አሰጣጥና አጠቃቀም ማንዋል ቁጥር 60/2013

አዲስ አበባ
ሰኔ 17/2006

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ

## በጋራ ህንፃ /ኮንደምንየም ቤት/ ለከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች/ሀኪሞች/ አሰጣጥና አጠቃቀም ማንዋል

***<u>መግቢያ</u>***፡-

የሀገራችን የጤና ፖሊሲ በመከላከል ላይ የተመሰረተ እና የራሱን ጤና ሊያመርት የሚችል ሕብረተሰብ መፍጠር ነው፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ በከተማዋ የሚስተዋለውን ከፍተኛ የጤና ችግር ለመቅረፍና ለሕብረተሰቡ ደረጃውን የጠበቀ፣ጥራት ፣ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለውን የጤና አገልግሎት ለማቅረብ ይቻል ዘንድ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የተለያዩ የሆስፒታል ማስፋፊያ ግንባታዎችን በማከናወን፣አዳዲስ ሆስፒታሎችን እና ጤና ጣቢያዎችን በመገንባት ከፍተኛና ውጤታማ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡

የጤና ተቋማትን ከማስፋፋት ባሻገር የተለያዩ ደረጃ ያላቸውን እስፒሻሊስት እና ጠቅላላ ሐኪሞችን እየሰጡ ያለውን የጤና አገልግሎት ጥራት ለማስጠበቅ ከፍተኛ እርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በመሆኑም በየሆስፒታሉ ተመድበው እየሰሩ ያሉትንና ወደፊትም በዝውውርም ሆነ በቅጥር ወደ አዲስ አበባ ጤና ተቋማት/ የሚመደቡ ከፍተኛ ባለሙያዎችን /ሐኪሞችን ተቀብሎ በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩና ሆስፒታሎቻችንም ለሀኪሞች ምቹና ተስማሚ የስራ ቦታ እንዲሆኑ እንዲሁም ከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች በተመደቡበት ቦታ ተረጋግተው ለረዥም ጊዜ በሙያቸው ሕብረተሰቡን እንዲያገለግሉ የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን እንዲከበሩላቸው ተደርጓል፡፡ ከነዚህ ጥቅማጥቅሞች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ለሐኪሞች የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ 250 ኮንደምንየም የጋራ መኖሪያ ቤት በመረከብ በወቅቱ ተመድበው እየሠሩ ለነበሩ ሐኪሞች በኪራይ እንዲገለገሉበት ተደርጓል፡፡ ወደፊትም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኤጀንሲ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን እየጠየቅን ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ ለሚመጣው የከፍተኛ ሐኪሞች አገልግሎት እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ እነኚህን የመንግስትና የሕዝብ ሃብት የሆኑትን ኮንደምንየም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተረክቦ በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር ስላለበት የቤቶቹን ስርጭት፣እርክክብ፣አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ የአፈፃፀም ማንዋል አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 1. ዓላማ

ይህ የአፈጻጸም ሠነድ እንዲዘጋጅ ያስፈለገበት ዋናው ጉዳይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ግንቦት 6 ቀን 2001 ዓ.ም ባካሄደው 26ኛ መደበኛ ስብሰባ ለከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች የመኖሪያ ቤት ችግርን ለመቅረፍ በአስተዳደሩ ከተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ በቁጥር 250 መኖሪያ ቤቶች በጤና ተቋማት ለሚሰሩ ስፔሻሊስት እና ለጠቅላላ ሀኪሞች በኪራይ እንዲሰጣቸው እና በየወሩ መክፈል የሚገባውን የኪራይ ክፍያ እየከፈሉ እንዲጠቀሙ በተወሰነው መሰረት ቅድሚያ ለስፔሻሊስት ሀኪሞች በመቀጠል ለጠቅላላ ሀኪሞች በዕጣ ቤት እንዲደርሳቸው ተደርጎ በተዘጋጀው ውል መሰረት ውሉን መፈረም ያለባቸው አካላት ማላትም የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ባለሙያው የሚሰራበት ጤና ተቋም እና የጤና ባለሙያው ግዴታዎች በግልጽ ተቀምጦ ሁሉም አካላት በፊርማቸው በማረጋገጥ ውል ተፈጽሟል፡፡ ከውሉ ባሻገር  በሂደት በአፈፃፀም የተለያዩ ክፍተቶች በመታየታቸው ለቢሮው የተለያዩ የስራ ሂደቶች፣ለጤና ተቋማትና ለከፍተኛ የጤና ባለሙያዎችን ተግባርና ኃላፊነት በመስጠት የታየውን ክፍተት ለመቅረፍ እና ለወደፊቱም ወጥ የአፈፃፀም ሰነድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው ፡፡

## 2. የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የተለያዩ የስራ ሂደቶች ተግባርና ኃላፊነት

### 2.1 የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ዋና የስራ ሂደት ተግባርና ኃለፊነት

1. በጤና ተቋማት የሚገኙ ስፒሻሊስት ሀኪሞችና ጠቅላላ ሀኪሞችን በተመለከተ በየጊዜው ወቅታዊ መረጃ መያዙን ይከታተላል፤
2. ከየተቋማቱ የሚላኩ የድጋፍ ደብዳቤዎችን በማየት በሪከርድነት እንዲያዝ ወደ ሰው ሀብት ልማት ደጋፊ ያስራ ሂደት ይመራል፣ይከታተላል፤
3. የህክምና አገለግሎት አሰጣጥ ንዑስ የስራ ሂደት መሪ ቤቶች በዕጣ በሚወጣበት ጊዜ የኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ይመራል፤
4. በዕጣ ተለይተው ቤት ከደረሳቸው ባለሙያዎች እና ከጤና ተቋማተት ጋር በጋራ በሚደረገው ውል ላይ ቢሮውን በመወከል የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ም/ቢሮ ኃላፊ ይፈርማሉ፤
5. በየጊዜው ከጤና ተቋማት በተለያዩ ምክንያት የሚለቁ ጠቅላላ ሃኪሞችና እስፔሻሊስት ሓኪሞች ወቅታዊ መረጃ/ዝርዝር/ መያዙን ይከታተላል፤

### 2.2 የግዢና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት ተግባርና ኃላፊነት

1. ከቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት የተሰጡና የሚሰጡ የኮንደምንየም ቤቶችን ይረከባል፤

2. ስለተረከባቸው ቤቶች ሙሉ መረጃ በሀርድና ሶፍት ከፒ ይይዛል/ የኮንደምንየም ሳይት፣የብሎክ ቁጥር፣የቤት ቁጥር፣ ወዘተ................/
3. ዕጣ ወጥቶላቸው ውል ለተዋዋሉ ሀኪሞች ቤቱን ባለበት ሁኔታ የተጠቀሰውን ቤት በመረካከቢያ ሰነድ ያስረክባል፤
4. ከጤና ተቋማት በማናቸውም ምክንያት ከሚለቁ ሀኪሞች ላይ የኮንደምንየም ቤቱን ይረከባል፣ስለመረከቡም ማረጋገጫ ይሰጣል፤ለቢሮው የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ም/ቢሮ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፤
5. የተለቀቁ ቤቶችን በተመለከተ ወዲያውኑ በሌላ ሀኪም ካልተከራየ ቤቱ አለመከራየቱን ለቤቶች ልማት ጽ/ቤት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤
6. ከጤና ተቋማት የሚላከለትን የከፍያ ሠነድ ከእያንዳንዱ ጤና ባለሙያ በመዝገብ/በስቶክ ካርድ አዘጋጅቶ መያዝ ይኖርበታል/ አባሪ 1 ተያይዟል/
7. ቢሮው የተረከባቸውን የኮንደምንየም ቤቶች በተመለከተ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ ያካሂዳል፤ሪፖርት ለቢሮ ኃላፊ ያቀርባል፤
8. ቤቶች በዕጣ በሚወጣበት ጊዜ የኮሚቴ አባል በመሆን ይሳተፋል፤
9. የቤት እደሳ ጥያቄ ሲቀርብ ጥያቄውን በአግባቡ ተቀብሎ ከቤቶች ልማት ፕሮጅክት ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር መፍትሄ ይሰጣል፤

**2.3 <u>የሰው ኃብት ልማት ደጋፊ የስራ ሂደት</u>**

1. የስፒሻሊስትና የጠቅላላ ሀኪሞችን የሰው ሀብት ብዛት በየተቋማቸው በመለየት መረጃ በሀርድና ሶፍት ኮፒ ይይዛል፤
2. ከህክምና አገልግሎት /ከጤና ተቋማት የሚላክለትን የድጋፍ ደብዳቤ መረጃ ይይዛል፣ መረጃውን አጠናቅሮ ለዕጣ አወጣጥ ስርዓት እንዲቀርብ ያደርጋል፤
3. ሀኪሞች በማንኛውም ምክንያት ከስራቸው በሚለቁበት ጊዜ የተረከቡትን ቤት ስለመመለሳቸው/ማስረከባቸው ማረጋገጫ እስካልቀረበ ድረስ የመልቀቂያ ጥያቄውን አያስተናግድም፤
4. ቤቶቹ በዕጣ በሚወጠጡበት ጊዜ የኮሚቴው ጸሐፊ በመሆን ያገለግላል ቃለጉባኤ ይይዛል፤
5. ዕጣው የወጣለት ባለሙያ ቤቱን ከግዢና ንብረት /አስ/ጠ/አገ/ደጋፊ የስራ ሂደት እንዲረከብ አስፈላጊው ቅድመ ርክክብ ሁኔታ መሟላቱን አረጋግጦ የውሉን ቅጂ በመሸኛ ያስተላልፋል፤
6. በየጊዜው ባለሙያዎች ሲለቁ ወቅታዊ መረጃ ይይዛል፤ለኃላፊዎች ሪፖርት ያቀርባል፤
7. ለባለሙያዎች ጥቅማ ጥቅም እንዲከበር አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

## 2.4 የውስጥ ኦዲት ደጋፊ የስራ ሂደት ተግባርና ኃላፊነት

1. የኮንደምንየም ቤት ዕጣ ወጥቶላቸው ውል ፈጽመው ቤት የተረከቡ ሀኪሞች የቤት ኪራይ በአግባቡ ስለመክፈላቸው በአስፈላጊው ጊዜ በኦዲት የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፤
2. በኦዲት የተደረሰበትን ግኝት ለቢሮ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፤
3. የስራ ሂደቱ ኃላፊ/ተወካይ የኮንደምንየም ቤት በዕጣ ሲወጣ በታዛቢነት ይገኛል፤

### 2.5. የህግ አገልግሎት ተግባርና ኃላፊነት

1. የጋራ ህንፃ /ኮንደምንየም ቤት መገልገያ የሚሆን የኪራይ ውል ያዘጋጃል/ያሻሽላል፤
2. በገቡት ውል መሰረት ያልተፈጸሙ ጉዳይ ካለ ከሚመለከተው ክፍል በሚደርሰው መረጃ መሰረት በህግ አግባብ ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል ፤
3. በህግ የሚሰጡ ውሳኔዎችን ለቢሮ ኃላፊ ሪፖርት ያደርጋል፤
4. የህግ አገልግሎቱ ኃላፊ/ተወካይ የኮንደምንየም ቤቱ በዕጣ ሲሰጥ በታዛቢነት ይገኛል፤

## 3 / የጤና ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

1. ኮንደምንየም ቤት ማግኘት የሚገባቸውን ሀኪሞች ስም እና የድጋፍ ደብዳቤ ለቢሮው ያስተላልፋል፤
2. ዕጣ ወጥቶላቸው ውል ተዘጋጅቶ የተላከለትን የጤና ተቋሙን ድርሻ ላይ የተቋሙ የበላይ አመራር ውሉ ላይ ይፈርማል ፤
3. የቤቱን ኪራይ ዋጋ ዕጣ ወጥቶላቸው ከተዋዋሉ ሀኪሞች ላይ ከወር ደሞወዝ እየቀነሰ በየወሩ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት በከፈተው የባንክ አካውንት በየወሩ የማስገባት ኃላፊነት አለበት፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ/3 እንደተጠበቀ ሆኖ ለተከራይ የኪራይ ደረሰኝ ይሰጣል፤ የየወሩን ሪፖርት ለጤና ቢሮ ያቀርባል፤
5. በማንኛውም ምክንያት ስራውን የሚያቋርጥ ሀኪም ቤቱን ለቢሮው ሳያስረክብና ማስረጃ ከቢሮው እስካልተሰጠ ድረስ የመልቀቂያ ጥያቄውን መስተናገድ የለበትም፤በተጨማሪም የቤት ኪራይ ሂሳብ ዕዳ የሌለበት መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ/5 የተገለፀው ሂደት ሳይከተል ተቋሙን በለቀቀ ሀኪም ምትክ የዕጣ አወጣጥ ሥርዓቱን ሳይከተል / ከቢሮው እውቅና ውጪ ለሌላ ሀኪም የኮንደምንየም ቤት መስጠት ወይም ማስተላለፍ አይቻልም፤
7. አዲስ የሚቀጠሩና የሚለቁ ባለሙያዎችን መረጃ ለቢሮው በየጊዜው ያቀርባል፤

## 4/ የጤና ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት

1. በዕጣ የደረሰውን የኮንደምንየም ቤት ከቢሮ የግዢና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት ይረከባል፤
2. በተከራየው ቤት ውስጥ ለተጠቀመበት የውኃ፣ የመብራትና የስልክ ፍጆታ ሂሳብ የመክፈል ግዴታ አለበት፤እንዲሁም ቤቱን ሲለቅ ከዕዳ ነፃ ለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፤
3. በኪራይ የተረከበውን ቤት ለሌላ 3ተኛ ወገን ማስተላለፍ ስም ማዛወር አይችልም፤

4. የተከራየውን ቤት የማቴርያልና የቅርፅ ለውጥ ሳያደርግ በራስ ወጪ ቢሮውን በማስፈቀድ እድሳት ማከናወን ይችላል ፤ሆኖም ላወጣው ወጪ ቢሮው ምንም ዓይነት ማካካሻ አይሰጥም፤
5. የተከራዩትን ቤት በጥንቃቄ በመያዝ ሲለቁም ባለበት ሁኔታ የማስረከብ ግዴታ አለበት፤
6. ቤቱ ላይ ለሚደርስ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ወቅት ወዲያውኑ ለቢሮው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፤
7. ኪቢሮው ወይም አግባብ ካለው አካል ሳያስፈቅድ የመኖሪያ ቤቱን ይዘትና ቅርፅ መለወጥ አይቻልም፤
8. በገባው የውል ግዴታ መሰረት መፈፀም ይጠበቅበታል፤ከስራ ሲለቁ ቤቱን ለቢሮው መመለስ እና ማስታወቅ አለበት፤
9. በጋራ ህንፃ ነዋሪዎች ማህበር የሚወጣውን የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ የማክበር ግዴታ አለበት፤
10. የጋራ ህንጻ አጠቃቀምና አኗኗርን አስመልክቶ ለወጡ ህጎች ተገዢ መሆን አለበት፤

**5/ <u>ልዩ ልዩ ጉዳዮች</u>**

1. ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኤጀንሲ፤ ቢሮው የኮንደሚንየም ቤት ሲረከብ ቤቶቹ ለባለሙያዎቹ የሚተላለፉት በዕጣ ብቻ ነው፤
2. የዚህ አንቀፅ ን.አንቀፅ 2 የተገለጸው ቢኖርም በተለያየ ምክንያት የተለቀቁ ቤቶች ሲኖሩ ከየጤና ተቋሙ በሚላከው ደብዳቤ መሰረት በጤና ተቋሙ የቅጥርና የአገልግሎት ጊዜያቸው ታሳቢ ተደርጎ እንደቅደም ተከተላቸው የሚስተናገዱ ይሆናሉ፤
3. በዕጣ አወጣጡ ሥርዓት ጊዜ የሚከተሉት አባለት የተገኙበት መሆን ይገባዋል፡-
    I. የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ንዑስ የስራ ሂደት መሪ..........................ሰብሰቢ
    II. የሰው ሀብት ልማት ደጋፊ የስራ ሂደት .................................................. ፀሐፊ
    III. የግዢ፣ንብረትአስ/ጠቅ/አገ/ደጋፊ የስራሂደት ......................................... አባል
    IV. የውስጥ ኦዲት ደጋፊ የስራ ሂደት ............................................................ ታዛቢ
    V. የህግ አገልግሎት ....................................................................................... ታዛቢ
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሱት የኮሚቴ አባላት በወቅቱ ስለተፈፀመው ድርጊት ቃለ-ጉባኤ ይይዛሉ ፤የተወሰነውን ውሳኔ ለሚመለከተው ያስተላልፋሉ፤
5. ይህንን የአፈፃፀም ማንዋል ከዛሬ ሰኔ 17 ቀን /2006 ዓም ጀምሮ ሁሉም አካላት ተፈፃሚ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ**

**አዲስ አበባ**

**ሰኔ/2006 ዓ.ም**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ**

**በጋራ ህንፃ /ኮንደምንየም ቤት/ ለከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች/ሀኪሞች/ አሰጣጥና አጠቃቀም ማንዋል**

**ማሻሻያ 2007**

**መግቢያ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የመንግስትና የሕዝብ ሃብት የሆኑትን ኮንደምንየም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ተረክቦ በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር ስላለበት የቤቶቹን ስርጭት፣እርከክብ፣አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ የአፈፃፀም ማንዋል አውጥቶ ተግባራዊ ማድረጉ የሚታወቅ ነው፡፡ ለዚህ የአፈጻጸም ማዋንል ለማዘጋጀት መነሻ የሆነው፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ግንቦት 6 ቀን 2001 ዓ.ም ባካሄደው 26ኛ መደበኛ ስብሰባ ለከፍተኛ የጤና ባለሙያዎች የመኖሪያ ቤት ችግርን ለመቅረፍ በአስተዳደሩ ከተገነቡ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ በቁጥር 250 መኖሪያ ቤቶች በጤና ተቋማት ለሚሰሩ ስፔሻሊስት እና ለጠቅላላ ሀኪሞች በኪራይ እንዲሰጣቸው እና በየወሩ መከፈል የሚገባውን የኪራይ ክፍያ እየከፈሉ እንዲጠቀሙ በተወሰነው መሰረት ቅድሚያ ለስፔሻሊስት ሀኪሞች በመቀጠል ለጠቅላላ ሀኪሞች በዕጣ ቤት እንዲደርሳቸው ለማድረግ ነበር፡፡

ስለሆነም የአፈጻጸም ማዋንሉን በዚሁ አግባብ ማሻሻል በማስፈለጉ ይህ ማሻሻያ በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ወጥቷል፡፡

**ማሻሻያ**

1. የአፈጻጸም ማንዋሉ አንቀጽ 5 ተራ ቁጥር 2 ተሰርዞ በሚከተለው ተሻሽሏል “የዚህ አንቀፅ ን.አንቀፅ 2 የተገለጸው ቢኖርም በተለያየ ምክንያት የተለቀቁ ቤቶች ሲኖሩ ከየጤና ተቋሙ በሚላከው ደብዳቤ መሰረት በጤና ተቋሙ የቅጥርና የአገልግሎት ጊዜያቸው ታሳቢ ተደርጎ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ስፔሻሊስት ሀኪሞች ዝርዝር ከዚህ በታች የተገለፁት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ለሌሎች ስፔሻሊስት ሀኪሞች እንደቅደም ተከተላቸው የሚስተናገዱ ይሆናል በቀጣይ ለአጠቃላይ ሀኪሞች የሚስተናገዱ ይሆናል ”
   የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጣቸው
   - የፅንስና የማህፀን ስፒሻሊስት
   - የአጠቃላይ ቀዶ ጥገና ስፔሻሊስት
   - የነርቭና የጀርባ አጥንት ስፔሻሊስት
   - የተቋም ኃላፊ ለሆነ ሀኪም( ቢሮው በኃላፊነት የሚያመጣቸው ከሆነ) ነው፡፡

**አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ**

**አዲስ አበባ**

**ነሀሴ/2007 ዓ.ም**